# <u>የምህረት አሰጣጥና አፈፃፀም አዋጅ አጭር ማብራሪያ</u>

## 1. <u>መግቢያ</u>

ምህረት የሀገርን ሰላምና ደህንነት ለማረገጥ በተወሰኑ የወንጀል አይነቶችና በአንድ ደረጃ ለሚገኙ ተጠርጣሪዎች ወይም ወንጀለኞች ላይ ምርመራ ወይም የክስ ሒደት ከማስቀጠል ወይም ቅጣትን ከማስፈፀም ይልቅ ምህረት የተሻለ ውጤት ያመጣል ተብሎ ሲታሰብ የሚሰጥ ነው።

አንዳንድ ፀሐፊዎች እንደሚሉት በ404 ምዕተ ዓመት በግሪክ አቴንስ የመጀመሪያው ምህረት እንደተሰጠ ያሰቀምጣሉ። በአሜሪካ በ1788 ዓ.ም የመጀመሪያው ምህረት በፕሬዘዳንቱ አማካኝነት እንደተሰጠ ይነገራል። በደቡብ አፍሪካ የአፓርታይድን አገዛዝ ማብቃት ተከትሎ በወቅቱ ለተፈፀሙ የወንጀል ድርጊቶች ምህረት ለማድረግ የእውነትና እርቅ አፈላላጊ ኮሚሽን (truth and reconciliation commission) ተቋቁሞ በፕሬዝዳንቱ አማካኝነት ምህረት ተደርጓል። በኡጋንዳም በየጊዜው እንደየጉዳዩ እየታየ የሕግ አውጪው በሕግ ምህረት ይሰጣል።

Addis Standard

በብዙ ሀገራት ልምድ ለማየት እንደሚቻለው በአብዛኛው ምህረት የሚሰጠው መንግስትን በኃይል ለመገልበጥ ከሚደረግ የወንጀል ድርጊት በኋላ፣ ከእርስ በርስና ዓለም አቀፍ ጦርነት በኋላ የሚኖሩ ፖለቲካዊ ብጥብጦችንና አለመግባባቶች ለማርገብ፣ በብጥብጡ ምክንያት የተከፋፈለን ማሕበረሰብ አንድነት ለመመለስ መጠነኛ የመንግስትንና የሀገር ሰላም የማደፍረስ ድርጊት ለፈፀሙና ወደ ሰላማዊ አኗኗር ለመመመለስ ፍቃደኛ ለሆኑ ሰዎች ነው።

በመሆኑም በኢትዮጵያ ውስጥ ሰላምና መረጋጋትን የሚያደፈርሱ ሁኔታዎች በሚፈጠሩበት ወቅት የማሕበረሰቡን ሰላም እና ደህንነት ለማረጋገጥ እንዲሁም ፖለቲካዊ፣ ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በተሻለ መልኩ ለመጠበቅ ምህረት መስጠት የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ ምህረት የሚሰጥበትን ሥነ-ሥርዓት በሕግ መደንገግ ስለሚያስፈልግ የምህረት አሰጣጥና አፈጻጸም ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ማውጣት አስፈላጊ ይሆናል። በዚህም መሠረት አዋጁ በአራት ክፍሎችና በአስራ ስድስት አንቀፆች ተከፋፍሎ ተዘጋጅቷል።

## 2. <u>የረቂቅ አዋጁ ዝርዝር ይዘት</u>

### ሀ/ <u>ጠቅላላ</u>

የአዋጁ ክፍል አንድ ጠቅላላ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን አንቀጽ አንድ የአዋጁን አጭር ርዕስ ይዟል። አንቀጽ ሁለት ደግሞ በአዋጁ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉና ትርጉም ያስፈልጋቸዋል የተባሉ ቃላቶችን ትርጓሜ ያስቀምጣል። አንቀጽ 3 የአዋጁን የተፈፃሚነት ወሰን የሚያስቀምጥ ሲሆን፣ አዋጁ በማንኛውም የወንጀል ዓይነቶች፣ ተጠርጣሪዎች ወይም ፍርደኞች ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን ተመልክቷል። በሌላ በኩል አዋጁ የሰው ዘር በማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ መውሰድ፣ በአስገዳጅ ሰውን መሰወር እና ኢ-ሰብአዊ የድብደባ ወንጀሎች ላይ ተፈጻሚ እንደማይሆን በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ላይ በግልጽ ተደንግጓል።

## ለ/ <u>ስለ ምህረት ቦርድ</u>

የረቂቅ አዋጁ ክፍል ሁለት ከአንቀጽ 4-8 ሲሆን በአንቀጽ 4 የምህረት ቦርድ ተመስርቷል። በአብዛኛው ምህረት የሚሰጠው የአገርን ሰላምና መረጋጋት አደጋ ላይ ለሚጥሉ የወንጀል ዓይነቶች ስለሆነ የቦርዱ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲሆን ተደርጓል። አንቀጽ 5 የምህረት ቦርዱን አባላት ስብጥር የያዘ ነው። ምህረት ከወንጀልና ቅጣት እንዲሁም ከሰላምና ደህንነት ጋር የተቆራኘ በመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የምህረት ቦርዱ ሰብሳቢ እንዲሆን ተደርጓል። በአብዛኛው ምህረት የሚሰጠው የሀገርን ሰላም እና መረጋጋት አደጋ ውስጥ ከሚጥል የወንጀል ድርጊት በኋላ በመሆኑ ተገቢውን ውሳኔ ለማስተላለፍና የተፈለገውን ውጤት ለማግኘት የተለያዩ የመንግሥት ሥራ አስፈጻሚ አካላትና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ተቋማትና ግለሰቦች በሂደቱ እንዲሳተፉ ማድረግ ተገቢ ነው። በዚህም መሰረት የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር፣ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር፣ የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ዋና ዳይሬክተር፣ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚወከል አንድ ዳኛ፣ መልካም ሥነ-ምግባር ያላቸው በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ ሁለት ሰዎች የቦርዱ አባላት እንዲሆኑ ተደርጓል።

የረቂቅ አዋጁ ከአንቀጽ 6-8 ስለ ምህረት ቦርዱ ሥልጣን እና ተግባር፣ የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ - ሥርዓት እና ስለ ቦርዱ ጽሕፈት ቤት ይደነግጋል። ቦርዱ የምህረት ጥያቄዎችን ይቀበላል፣ ይመረምራል የውሳኔ ሀሳብ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀርባል። ውሳኔውንም በአብላጫ ድምፅ ያስተላልፋል። ምህረት በተወሰነ ጊዜ ለሚፈጸሙ ድርጊቶች የሚሰጥና የሙሉ ጊዜ ሥራ የማይፈልግ ከመሆኑ አንጻር እንዲሁም ለቦርዱ አዲስ ጽሕፈት ቤት በማደራጀት በመንግሥት

Addis Standard

ላይ አስተዳደራዊ ወጪ ከማስከተል ይልቅ በቦርዱ ሰብሳቢ መስሪያ ቤት ማለትም በፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ውስጥ በተደራጀው የይቅርታ ቦርድ ጽሕፈት ቤት የቦርዱ ጽሕፈት ቤት እንዲሆን ማድረግ የተሻለ አማራጭ እንዲሆን ተደርጓል።

**ሐ/ <u>ስለ ምህረት አሰጣጥ እና አፈፃፀም</u>**

ይህ ክፍል ከአንቀጽ 9 እስከ 12 የያዘ ሲሆን አንቀጽ 9 ምህረት የሚሰጥባቸውን ጉዳዮች የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሀገርን ሠላምና ደህንነት ማስጠበቅ ካለው ኃላፊነት እንዲሁም ምህረት ከሚያሰጡ የወንጀል ድርጊቶች ጋር ካለው ቅርበት አንፃር በራሱ ተነሳሽነት ወይም ከክልሎች በሚቀርብ ጥያቄ ምህረት የሚሰጥባቸውን ወንጀሎች እና በወንጀል የተጠረጠሩ ወይም የወንጀል ፍርድ የተላለፈባቸው ሰዎች ለይቶ ለቦርዱ እንዲያቀርቡ ያደርጓል።

የአዋጁ አንቀጽ 10 ደግሞ ምሕረትን ለመስጠት ከግምት ውስጥ የሚገቡ ሁኔታዎችን የሚያስቀምጥ ሲሆን ምህረት ለመስጠት ምህረት የተጠየቀበት የወንጀል ድርጊት በሀገር ሉአላዊነት ላይ የሚያስከትለው ወይም ያስከተለው ተፅዕኖ፣ ሰላም እና ደህንነት ለማረጋገጥ ምህረት የተሻለ አማራጭ ስለመሆኑ እና ምህረት የሚደረግላቸው ሰዎች ወደ ሰላማዊ ሕይወት ለመመለስ የሚያሳዩት ፍላጎት ከግምት ውስጥ እንደሚገባ በግልጽ ያስቀምጣል።

Addis Standard

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 11 ምሕረት የሚሰጥበትን አግባብ የሚያስቀምጥ ሲሆን ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ከምህረት ቦርዱ የቀረበለትን የውሳኔ ሐሳብ ከተቀበለ በጉዳዩ ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ረቂቅ የምሕረት አዋጅ እንዲያዘጋጅ ያደርጋል። በመቀጠልም ረቂቅ የምሕረት አዋጁ እንደማንኛውም ሕግ ተገቢውን የሕግ አወጣጥ ሂደት ተከትሎ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲጸድቅ የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ምህረቱን ያስፈፅማል። ምሕረቱ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በኩል እንዲታይ የሚቀርብበት ምክንያት በኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 230(1) ላይ የምሕረት አሰጣጥ በሕግ እንደሚወሰን በመደንደጉ ነው። ሕግ የማውጣት ሥልጣን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመሆኑ ምሕረቱ በሌላ አካል እንዲታይ ማድረግ የሚቻል ባለመሆኑ ነው።

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 12(1)(ሀ-መ) ምህረት ከወንጀልና ከፍትሐ ብሔር ተጠያቂነት አንፃር የሚያስከትለውን ውጤት ያስቀምጣል። በዚህም መሠረት ምርመራ ወይም ክስ እንዳይጀመር ወይም የተጀመረ ምርመራ ወይም ክስ እንዳይቀጥል ወይም ቅጣት እንዳይፈፀም ያደርጋል፤ እንዲሁም የጥፋተኝነት ውሳኔም እንዳልነበረ ያስቀጥራል። በተጨማሪም የፍትሐ ብሔር

ተጠያቂነትን በተመለከተ በምህረት አዋጁ በልዩ ሁኔታ ካልተገለፀ በስተቀር ለመንግስት ሊከፈል የሚገባውና ገና ያልተከፈለ ኪሳራ በምሕረት ቀሪ እንደሚሆን በግልጽ ተቀምጧል። ነገር ግን በፍትሐ ብሔር በኩል የጠፋውን እንደነበረ የመመለስና በተበዳዩ ላይ ለደረሰው ጉዳት የሚከፈለውን ካሳና ኪሳራ እንደማያስቀር በዚሁ አንቀጽ 12(2) ላይ ተደንግጓል።

### መ/ <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 13 የምህረቱን ዓላማ ለማሳካት ትብብር የተጠየቀ ሰው የመተባበር ግዴታ እንዳለበት ይደነግጋል። የረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 14 ደግሞ ከአዋጁ ድንጋጌዎች ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሠራር ተፈጻሚነት እንደሌለው ያስቀምጣል። ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዱ ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣንም እንደቅደም ተከተላቸው የሚኒስትሮች ምክር ቤትና ቦርዱ ሊያወጡ የሚችሉ መሆኑ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 15 ተመልክቷል። በመጨረሻም አዋጁ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ እንደሚሆን በአንቀጽ 16 ላይ ተቀምጧል።

## 3. <u>ማጠቃለያ</u>

የአዋጅ ምሕረት ሕገ መንግስታዊ ይዘት ያለው በአብዛኛው የፖለቲካ ጥፋቶችን፣ ሀገር መክዳት፣ የአመፅ ወንጀሎችን እና በሀገርና በመንግስት ላይ አመፅ ማነሣሣት ወንጀል ለፈፀሙና በሕግ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ወደ ሰላማዊ ኑሮአቸው ተመልሰው የመንግስትን ሕግ እና ሥርዓት ለማክበር ግዴታ ለሚገቡ ጥቂት ወይም መላው ወንጀለኞች መንግስት ያለፈውን ጥፋታቸውን ሙሉ በሙሉ ስሪየት የሚያደርግበት ሥርዓት ነው። ምህረት መብት ሳይሆን የሀገርን ሰላምና ደህንነት ለማረገጥ በተወሰኑ የወንጀል ዓይነቶችና በአንድ ደረጃ ለሚገኙ ተጠርጣሪዎች ወይም ወንጀለኞች ላይ ምርመራ ወይም የክስ ሒደት ከማስቀጠል ወይም ቅጣትን ከማስፈፀም ይልቅ ምህረት የተሻለ ውጤት ያመጣል ተብሎ ሲታሰብ የሚሰጥ ነው።

Addis Standard

ከተለያዩ ሀገራት ልምድ ለማየት እንደሚቻለው በአብዛኛው ምህረት የሚሰጠው መንግስትን በኃይል ለመገልበጥ ከሚደረግ የወንጀል ድርጊት በኋላ፣ ከእርስ በርስና ዓለም አቀፍ ጦርነት በኋላ የሚኖሩ ፖለቲካዊ ብጥብጦችንና አለመግባባቶች ለማርገብ፣ በብጥብጡ ምክንያት የተከፋፈለን ማሕበረሰብ አንድነት ለመመለስ መጠነኛ የመንግስትንና የሀገር ሰላም የማደፍረስ ድርጊት ለፈፀሙና ወደ ሰላማዊ አኗኗር ለመመለስ ፍቃደኛ ለሆኑ ሰዎች ነው።

በመሆኑም በሀገራችን ውስጥ ሠላምና መረጋጋትን የሚያደፈርሱ ሁኔታዎች በሚፈጠሩበት ወቅት የማሕበረሰቡን ሰላም እና ደህንነት ለማረጋገጥ እንዲሁም ፖለቲካዊ፣ ማሕበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም በተሻለ መልኩ ለመጠበቅ ምህረት መስጠት የሚያስችል ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ነው። የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 28 በስብዕና ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በምህረት እንደማይታለፉ የሚደነግግ ሲሆን፤ በሌሎች የወንጀል ጉዳዮች ምህረትን በህግ መስጠት የሚቻል ስለመሆኑ አመላካች ነው። የ1996 ወንጀል ሕጉ በሕግ ምህረት መስጠት የሚቻልበትን ሁኔታ የሚደነግግ ቢሆንም ምህረትን የሚመለከተው ሥነ-ሥርዓት ሕግ እስከ አሁን በሕግ አውጪው ወጥቶ ሥራ ላይ አልዋለም።

በመሆኑ ምህረትን በተመለከተ በወንጀል ሕግ የተደነገገውን ከሕገ-መንግሥቱ ጋር በማጣጣም ምህረት የሚሰጥበትን ሥነ-ሥርዓት በሕግ መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በዚህም መሠረት  የሚኒስትሮች ምክር ቤት ረቂቅ አዋጁን መርምሮ ውሳኔ በመስጠት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲጸድቅ እንዲተላልፍ ከዚህ አጭር ማብራሪያ ጋር ቀርቧል።

Addis Standard